በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ.200144

ቀን፡- 02/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ እማሆይ አዛል አይናለም

ተጠሪ፡ አቶ ምህረት በላይ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የስጦታ ውል እንዲፈርስ የቀረበ ክስ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ቡሬ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ እንዲሁም የቡሬ ወረዳ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ጽ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የአመልካች ክስ ይዘት ባጭሩ ለተጠሪ ያደረግሁለት የሥጦታ ውል በመንፈስ ልልነት እና በዕድሜ የገፋሁ አቅመ ደካማ በመሆኔ ምክንያት ከፈቃዴ ውጭ ህጉን ሳይከተል ያደረግሁት በመሆኑ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር የስጦታ ውሉን ያፀደቀ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ አመልካች በፈቃዷ ስጦታውን ያደረገችለት መሆኑን እና ክሱ የቀረበው የአመልካች ልጆች ከቅን ልቦና ውጭ በሆነ ሁኔታ መሬቱን ለመውሰድ በማሰብ ነዉ፤የስጦታ ውሉ የሚፈርስበት የህግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር 2ኛ ተከሳሽም አመልካች

የራሷን ይዞታ በሙሉ ፈቃዷና ፍላጎቷ በወቅቱ በነበሩ ሽማግዎችና የመሬት ባለሙያዎች ባሉበት ግልጽ የስጦታ ውል  በህጉ መሰረት የተደረገ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ መስጠቱን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች በቀን 24/06/2005 ዓ.ም በቀበሌ ጽ/ቤት የመሬት ስጦታ ውል ላይ መፈረሟን አልካደችም፣የስጦታ ውሉ በሙሉ ፍላጎት ማመልከቻ አቅርባ እንዲታሰብበት ተደርጎ በቀበሌውም ማስታወቂያ ተለጥፎ ዉሉ የተፈፀመ መሆኑን በተጠሪ ምስክሮች በተገቢው ሁኔታ ተረጋግጧል፣ የአመልካች ምስክሮች ግን ስለስጦታ ውሉ የሚያውቁት የሌለ በመሆኑ ክሱን ማስረዳት አልቻሉም፣ስለዚህ አመልካች ስጦታ ያደረገችዉ በሙሉ ፍላጎቷና ፍቃዷ መሆኑን እንዲሁም የስር 2ኛ ተከሳሽም ስጦታውን ተቀብሎ ያፀደቀው በህጉ አግባብ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች የቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴ የሆኑት አመልካች ለተጠሪ መሬት ለመስጠት ፍላጎት ኖሯት ያቀረበችው ማመልከቻ እንደሌለ እና መሬቱ ባለበት ቦታ ያጣሩት ነገር እንደሌለ ገልፀው በተለይ 1ኛ ምስክር ተጠሪ ስጦታ ልትሰጠኝ ነው ብሎ ወረቀት ይዞ መጥቶ አመልካች አብራ ካልመጣች በሚል እንደመለሰው እና በዛው ሳይመጣ እንደቀረ የሰጠዉ ቃል እንዲሁም ተጠሪ የሚጠበቅበትን ቢያንስ 3(ሶስት) ዓመት አመልካችን ስለመጦሩ ማረጋገጫ ሳይቀርብ እና የወረዳው መሬት አስተዳደር ተጠሪ ያቀረቡት ማመልከቻ ላይ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ የለጠፈው ማስታወቂያ ማግኘት እንዳልቻሉ የገለፁ በመሆኑ የተደረገው የስጦታ ውል ህግና መመሪያውን ተከትሎ የተፈፀመ ነው ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ስጦታው ሊሻር ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የአመልካች ምስክሮች ስጦታ ሲደረግ እንደማያውቁ መናገራቸዉን፤ስጦታ ሲደረግ የነበሩት የተጠሪ ምስክሮች ቃል የሚያስተባብል ባለመሆኑ በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት ስጦታ ተደርጓል የተባለው አነጋገር የተሻለ ተቀባይነት ያለው ነው፣ ተጠሪ የህጉን መስፈርት አሟልቶ ስጦታ ተጠቃሚ ከሆነ በኋላ ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች አግባብ ባለው አካል አለመገኘታቸው ስጦታውን ሊያፈርስበት የሚገባ አይደለም፣ የመጦር ግዴታ የከፍተኛ ፍ/ቤት በራሱ አንስቶ የሰጠው

ዳኝነት ሲታይ አግባብ ሆኖ አልተገኘም በማለት የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ይታረምልኝ በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ላይ ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የስጦታ ውሉ በመስፈርት ረገድ ጉድለት ያለበት አይደለም፤አመልካች ስጦታውን ለማድረግ ያመለከተችበት ማመልከቻ እና ቃለጉባኤ ማግኘት ባይቻልም አመልካች በወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርባ ስጦታውን ያደረገች መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ እና ውሉ በማጭበርበር ወይም ከአመልካች ፈቃድ ውጭ በሆነ ሁኔታ ስለመፈፀሙ በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ የስጦታ ውሉ የሚፈርስበት ሁኔታ የለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፤ የስጦታ ውሉ የመሬት አስተዳደር ደንብ ቁ.51/99 እና የአፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 12/7/ ላይ የተመለከተውን ሂደት ሳይከተል፤የፍ/ህ/ቁ 881 መሰረት ስጦታው የግልጽ ኑዛዜ ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 2443 መሰረት ተቀባይነት የሌለው እና በስጦታ ቅጽ ላይ ተጎትቼ እንዲፈርም ተደርጎ የአንድ ዓመት ቆይታ ጠብቆ ሳይመዘገብ ለስጦታ ተቀባይ ማረጋገጫ ደብተር መስጠቱ እየታወቀ ውሉ የጸና ነው ሲል ውሳኔ መስጠቱ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአሁኑ አመልካች መሬት በስጦታ ለተጠሪ ለመስጠት ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ ባልሰጡበት እንዲሁም ተጠሪ የመጠር ግዴታ መወጣቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስጦታ ውሉ ሕጋዊ ነው ሊፈርስ አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነበትን አግባብ ከፍ/ሕ/ቁ 881 እና 2443 እንዲሁም ከክልሉ ገጠር መሬት አዋጅ ጋር በማገናዘብ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ባጭሩ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ተጠሪ በማባበልና በማስፈራራት ያለፈቃዴና ፍላጎቴ ወደ ቢሮ ወስዶኝ እጄን ጎትቶ ያስፈረመኝና ስጦታውም የጸደቀ ስለሆነ ውሉ ይፍርስልኝ የሚል እንጂ ተጠሪ ግዴታውን አልተወጣም ወይም አበል ከለከኝ አልተባለም፤ስለዚህ ግዴታውን አልተወጣም የሚል በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ስለሆነ አጣሪ ችሎቱ የመጦር ግዴታውን መወጣት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሚለው ጭብጥ

ተቀባይነት የለውም፤አመልካች በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የእርሷ ቤተሰብ አባል በመሆን ከ3 አመት በላይ በነፃ ሳገለግልና ስጦር እንደቆየሁ በግልጽ በማመን የስጦታ ውሉ እንዲደረግ በማመልከቻ ጠይቃ የተደረገ መሆኑ በአዋዋይ ሽማግሌዎች በመረጋገጡ፤ የስጦታ ውል በህግ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ የተደረገ መሆኑ ተረጋግጦና ተመዝግቦ ውሉ ፀድቆ የባለይዞታነት መብት በተጠሪ ስም የተላለፈ ስለመሆኑ አዋዋይ ሽማግሌ በሆኑት ምስክሮችና በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበንዉ አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የገጠር መሬት ስጦታ ዉል በመሬት አስተዳደር አካል ተመዝግቦና በመሬቱ ላይ የይዞታ መረጋገጫ ደብተር ለተጠሪ መሰጠቱ የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ሲሆን ይህ ዉል እንድፈርስ አመልካች ዳኝነት የጠየቁት የሥጦታ ዉሉ በመንፈሰ ልልነትና አቅመ ደካማነት የተደረገ ነዉ በሚል ምክንያት ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡

የስጦታ ዉል ማለት ሰጪዉ ለሌላ ሰዉ ችሮታ በማድረግ ሃሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ዉል ስለመሆኑና ስጦታ ማድረግ የሰጪዉ የግል ተግባር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2427 እና 2434 ይደነግጋል፡ከዚህ እንደምንገነዘበዉ ስጦታ ዉል የጸና ዉል እንዲሆን እንደማናቸዉም የዉል ጉዳዮች በዉል ህግ የተደነገገዉን መሰረታዊ መስፈርት አሟልቶ መገኘት ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡የስጦታ ዉሉ በህግ የተመለከተዉን መሰረታዊ መስፈርት እና ስለስጦታ ዉል የተደነገጉትን ደንቦች ኣላሟላም በሚል መብትና ጥቅሙ የተነካበት ወገን ዉሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ እንደሚችል ከዉል ህጎች ጠቅላላ ድንጋጌ እና ስለስጦታ ዉሎች ከተደነገገዉ ልዩ ከፍል መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሰረቱ አንድ ዉል እንዲፈርስ የሚደረገዉ ዉሉ የተቋቋመበት ሁኔታ ከመሰረቱ ግድፈት ሲኖርበት ነዉ፡፡ይኸዉም የተዋዋይ ወገን ለመዋዋል ችሎታ ወይም ፈቃድ ጉድለት ሲኖር ወይም የዉለታዉ ጉዳይ ህግን ወይም ግብረ ገብነት/ሞራል/ የሚጻረር ሲሆን ወይም በህግ የተደነገገዉን ፎርም ሳያሟላ ሲቀር ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላ ሁኔታ ዉሉ ጉድለት አለበት በሚል ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚችለዉ ወገን ማንነት እንደየምክንያቱ የሚለያይ መሆኑም በዚሁ ድንጋጌ ላይ ተመልክቷል፡፡

ይህ እንደ አጠቃላይ ሆኖ የስጦታዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልባቸዉ ልዩ ሁኔታዎች በህጉ አንቀጽ 2437 እስከ 2440 ላይ ተዘርዝረዋል፡፡በዚህም መሠረት የስጦታ ዉል ሊፈርስ የሚችለዉ ስጦታዉ በተደረገበት ወቅት ስጦታ አድራጊዉ የአእምሮ ችግር እንዳለበት ታዉቆ በፍርድ ክልከላ የተደረገበት (judicial interdiction) ወይም ስጦታዉ የተደረገዉ ስጦታ ሰጪዉ የፍርድ ክልከላ እንዲደረግበት ለፍርድ ቤት ጥያቄ ከቀረበ በኋላ ወይም ስጦታዉ ሲደረግ የስጦታ ሰጪዉ አእምሮ ጤነኛ አለመሆኑን የዉሉ ይዘት የሚያሳይ ሲሆን፣ ስጦታዉን ለማድረግ መነሻ የሆነዉ ምክንያት ከህግ ወይም ከሞራል ተቃራኒ ከሆነ፣ ስጦታዉ ሲደረግ ስጦታ ሰጪዉ በመንፈስ ጫና (undue influence) ስር መሆኑ ከተረጋገጠ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ስለሆነም የስጦታ ዉል እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰዉ ከእነዚህ ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንድ ሁኔታ መኖሩን የመግለጽ እና ይህንኑ የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ስጦታዉ እንዲፈርስ የጠቀሱት ምክንያት ስጦታ ያደረጉት በመንፈስ ልልነትና አቅመ ደካማነት በተጠሪ ጫና ተደርጎባቸዉ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች የግራቀኙን ማስረጃ መርምረዉ እና አመዛዝነዉ በዚህ ረገድ የአመልካች ምስክሮች ያስረዱት አሳማኝ ምክንያት አለመኖሩን አረጋግጠዋል፡፡በመሰረቱ የስጦታ ዉሉ የተደረገዉ በመንፈስ መጫን ነዉ የሚለዉን ፍሬነገር ጉዳይ የማስረዳት ሸክም የአመልካች ስለመሆኑ ህጉ ያስገነዝባል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2439፤2001/1/ እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 259 ድንጋጌዎችን ይመለከታል፡፡ይሁንና አመልካች በክሱ የጠቀሱት ሁኔታ ስለመኖሩ ወይም በስጦታ አድራጊዉ አእምሮ ላይ ተፅዕኖ ስለመኖሩ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ስለዚህም እንደክሳቸዉ አቀራረብ ዉሉ በጫና የተደረገ መሆኑን ማስረዳት ባልቻሉበት ሁኔታ በዚህ ምክንያት ዉሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት የለዉም፡፡ሌላዉ አመልካች መከራከሪያ የሥጦታ ዉሉ ፎርም የሚመለከት ነዉ፡፡ አከራካሪዉ የሥጦታ ዉል የተደረገዉ በ24/06/2005ዓ.ም መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡ የገጠር መሬት ባለይዞታ የይዞታ መብቱን በስጦታ ሌላ ሰዉ ሊያስተላለፍ የሚችል ስለመሆኑና መሟላት ያለባቸዉ ሁኔታዎች አስመልክቶ በወቅቱ ስራ ላይ የነበረዉ አማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 15 እና 17 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የዉሉን ፎርም አስመልክቶ የስጦታ ዉሉ በጽሁፍ መደረግ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡የአዋጁን አንቀጽ17/5/ይመለከታል፡፡እንዲሁም ስምምነቱ መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ባለዉ የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ እንዳለበትም ያመለክታል፡፡በተያዘዉም ጉዳይ ማስረጃ የመመርመርና ፍሬነገር ማረጋገጥ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች እንዳረጋገጡት

የመሬት ስጦታ ዉሉ የተደረገዉ በአካባቢ ሽማግሌዎችና በቀበሌዉ ጽ/ቤት ፊት በጽሁፍ የተደረገ ስለመሆኑና በአዋጅ እና የአዋጁን ማስፈጸሚያ ደንብ ተከትሎ ተገቢዉን ሂደት ተከትሎና ፎርማሊቲ ተሟልቶ ምዝገባና የይዞታ ማረጋገጫ በተጠሪ ስም የተከናወነ መሆኑን ያረጋገጡት ጉዳይ ስለመሆኑ ዉሳኔዉ ያሣያል፡፡ስለሆነም የገጠር መሬት ስጦታ ዉል አፈጻጸም በሚመለከት በልዩ ህጉ የተደነገገዉ ፎርምና ምዝገባ ስርዓት ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 881 እና 2443 የተደገገዉን አላሟላም የምባልበት ምክንያት የለም፡፡በዚህም ረገድ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ ሌላዉ ጭብጥ ተጠሪ አመልካችን ስለመጦሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሥጦታ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በሚመለከት ነዉ፡፡በመሰረቱ ይህ የክርክር ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት አዲስ ክርክር ነዉ በሚል በሰበር ላይ የቅሬታ ነጥብ ሆኖ መቅረቡ ተገቢነት እንደሌለዉ በመግለጽ ተጠሪ ተከራክሯል፡፡ከመዝገቡ እንደሚታዉ ተጠሪ አመልካችን የመጦር ግዴታ አልተወጣም በሚል ምክንያት የሥጦታ ዉሉ እንዲፈርስ አመልካች በግልጽ ዳኝነት ስለመጠየቃቸዉ መዝገቡ አያሣይም፡፡በዚህ ረገድ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ እንደሚያሣየዉ የመጦር ግዴታ አስመልክቶ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በራሱ ጊዜ ያነሳዉ እንጂ የአመልካች የክስ ምክንያት አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሻረበት አንዱ ምክንያትም የመጦር ግዴታን በሚመለከት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 329/1/ እንደተደነገገዉ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክርና አዲስ ነገር በይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት የለዉም የሚለዉ የክርክር አመራር መርህ ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ይህ መርህ ለሰበር ችሎትም ተፈጻሚነት እንዳለዉ እሙን ነዉ፡፡ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን ለመጦር ከስጦታ ዉሉ ወይም ከህግ የመነጨ ግዴታ ስለመኖሩ ገልጸዉ ዳኝነት ባልጠየቁበት ብሎም ግዴታዉን ማጓደል አለማጓደሉ የክርክር ምክንያት ሆኖ በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ ዉሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ ይህ ሰበር ችሎት የክርክር ጭብጥ አድርጎ የምወስንበት ስነስርዓታዊ መሰረት የለዉም፡፡ይሁንና የመጦር ግዴታን አስመልክቶ በማንኛዉም ጊዜ ዳኝነት ከመጠየቅ የሚገድብ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል የሥጦታ ዉሉ በጽሁፍ የተደረገ እና በሚመለከተዉ አካል የተመዘገበ መሆኑን በማረጋገጥ ዉሉ የሚፈርስበት ሌላ ህጋዊ ምክንያት መኖሩን አመልካች በተገቢዉ ማስረጃ ባለማስረዳታቸዉ ክርክራቸዉን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ

በግራቀኙ የቀረበዉን ክርክርና በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬነገር መሰረት በማድረግ መሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡በመሆኑም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10 ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ ዉሳኔዉ ህጉንና እና ስለገጠር መሬት ስጦታ ዉል አፈጻጸም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ የተደነገገዉን ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/48692 ላይ በ28/05/2011ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/03-84881 ላይ በ27/11/2012ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡ 2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

ሂ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነ ድ ለ ጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እ ንጂ 
ለ ፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም